www.ethiopianorthodox.org

# በመንፈስ ለሞቱ የትምህርት ትንሣኤ

በዚህ ዓለም ሁለት ዓይነት ምውታን
አሉ አንደኛ የዚህን ዓለም ኑሮ ፈጽመው
በሥጋ የሞቱ ሲሆኑ ፤ እነርሱም በመቃ
ብር ውስጥ ሆነው የሕይወትን ትንሣኤ
እስኪያገኙ ድረስ መናገር ማየት ፤ መስ
ማት የሚደረገውን ነገር ሁሉ ማወቅ አ
ይችሉም የደረቁ አጥንቶች ሆነዋልና ።
ሁለተኛ ደግሞ ትምህርትንና እውቀ
ቀትን በማጣት በጨለማ ድንቁርና የተቀ
በሩ ፤ ብርሃኑ ጨለማ ፤ ጨለማው ብር
ሃን የሆነባቸው ፤ ሜዳው ገደል ፤ ገደሉ
ሜዳ የሚመስላቸው ፤ ጣፋጩ መራራ፡
መራራው ጣፋጭ እየመሰላቸው የሚኖ
ሩ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወታቸው
የደረቀባቸው ምዕመናን ናቸው ።

ለምሳሌ በሾላ ውስጥ ያለ ትል እሱ ከ
ሚኖርበት ከሾላ ቅርፊት ውስጥ በቀር
ሌላ ዓለም ያለ ስለማይመስለው ደስ ብ
ሎት ይኖራል የትምህርት ጸጋ የተገፈፈ
ባቸው ፤ የእውቀት አድማስ የራቀባቸው
ሰዎችም ከአካባቢያቸው በቀር ሌላ አዲ
ስ ዓለም ሌላም የሥራ ሐገር ያለ አይመ
ስላቸውም ስለዚህ እንዲህ ላሉት ሰዎች
በትምህርት የዕውቀት ትንሣኤ ያሻቸዋ
ል የመንፈስ ተሐድሶም ያስፈልጋቸዋል
ምክንያቱም ትምህርት መንፈሳዊውን
ነገር ለማወቅና ለመቀበል ወደ ሥራ ዓ
ለምም ለመምራት የሚያስችል በመሆኑ
ነው ። ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ ትምህ
ርት የመልካም ነገሮች ምንጭ መሆኑን
ሊቃውንት ራሳቸውን ጠቅመው ሌላ
ውንም ጠቅመውበታል ።

ይህንንም የተገነዘበው ነቢዩ ሕዝቅ
ኤል ከትምህርትና ከዕውቀት የእግዚአ
አብሔር ቃል ከመስማት ተራቁተውና
ተማርከው የነበሩትን እስራኤል በሙታ
ን ፤ ባቢሎን በመቃብር ፤ ኑሮአቸው
ን በሸለቆ ሕይወታቸውን በደረቁ አጥን
ቶች መስሎ ትንቢት ሲናገር « እናንተ
የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ የእግዚአብ
ሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር ለ
እነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል እነሆ
ትንፋሽን አገባባችኋለሁ በሕይወትም
ትኖራላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ
ሆንኩ ታውቃላችሁ » ብሏል ። ትንቢተ
ሕዝቅኤል ምራፍ 37 ፤ 2 - 7

እንዳለውም እነዚህ አጥንቶች የወደ
ቁበት ሥፍራ ሸለቆ እንደመሆኑ መጠን
ውኃ የማይገኝበት የማይወርድበት ፤ ል
ምላሜ የማይታይበት ዝናብ የማያካፋ
በት ታላቅ በረሐ ስለ ነበረ በገዛ ጥረታ
ቸው ሕይወትን ለማግኘት አልቻሉም።
ሕዝቅኤል በሕይወት ትኖራላችሁ ያለው
ስለዚህ ነበር ። በእርግጥም የተማረኩት
ሕዝቦች በኃጢአት ጎስቁለው ስለነበር
ብዙ ነገር ያስፈልጋቸዋል ። ይኸውም
ሕይወት ስለሌላቸው አዲስ ሕይወት ፤ ት
ምህርት ፤ ንስሐ የእግዚአብሔርን ቃል
መስማት ሚጠት ፤ ነፃነት ያስፈልጋቸው
ነበር ።

ሕዝቅኤል የተናገረው ለተማረኩት
ቢሆንም ሁኔታው ተመሳሳይ በመሆኑ
እኛም የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት
ለመቀስቀስ ነው የተነሳነው ለምሳሊ ሊ
ቃውንት ትምህርት ሁለተኛ ፈጣሪ ነው
ይላሉ በእርግጥም ሰውን ሥጋዊ ሕይወ
ቱንም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወቱን እንደገ
ና ሊፈጥረው ፤ ሊያድሰው ሰው አድርጎ
ከእውቀት ሊወልደው የሚችለው ትም
ህርት ነው ይህም አላማ ሊሳካ የሚችለው
እንደ ሕዝቅኤል ያለ መልካም አስተማሪ
ካህን ሲገኝ ነው እንዲህ ያለው ካህን በ
በምድረ በዳ የወደቁትን ማይማን በት
ምህርት ሊያስነሳቸውና ሕይወታቸው
ንም በእውቀት ሊያድስላቸው ይችላል
በኃጢአት ሸለቆ ውስጥ ደርቆ የወደቀ
ውንም የምዕመናን ሕይወት በንስሐ አ
ድሶ በክርስቶስ ቃል ሕያው አድርጎ በ
መንፈስ ሙቀት ሰጥቶና አለምልሞ
የመንፈሱ ፍሬ እንዲያፈራ ሊያደርግ
ይችላል ።

ለምሳሌ ዶሮ ማርባት የምትወድ አ
ንዲት ሴት ነበረች እርሷም ከሠላሳ የሚ
በልጡ እንቁላሎችን ሰብስባ ለብዙ ቀን
አስቀመጠቻቸው እነሱም ሙቀት ከም
ትሰጣቸው እናታቸው ስለተለዩ በድን
ከመሆን በቀር ሕይወትን አግኝተው ሊ
ንቀሳቀሱና ጫጩት ሊሆኑ አልቻሉም
ሴትየዋም ነገሩ እንዳልተሳካላት ባየች
ጊዜ እንደገና ለእናታቸው አስታቀፈቻ
ቸው እነሱም ሙቀት ስላገኙ ከሦስት
ሣምንት በኋላ እንቁላሎቹ ወደ ጨጬት
ትነት ተለውጠውና ሕይወት አግኝተው
የእንቁላሉን ቅርፊት እናቲቱ ሰብራ አ
ወጣቻቸው አድገውም ትልልቅ ዶሮዎች
ሆኑላት ይህች ም ሴት ከመደሰቱዋም
ሌላ በእግዚአብሔር ፍጥረት አፈጣጠር
ና ሕይወት ሰጪ መሆኑንም አደነቀች።
ምእመናንም እንደ ሕዝቅኤል ያለ ካህ
ን የሚያስተምራቸው ካላገኙ ሕይወታ
ቸው ይቀዘቅዛል መንፈሳቸውም በድን
ይሆናል ተምረው ካወቁ ግን የመንፈስ
ሙቀት የሚሰጣቸው እንደ ዶሮሞ ከክ
ንፉ በታች የሚያቅፋቸው እናት አባት
የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላላቸ
ው የቀዘቀዘው ሕይወታቸው ይሞቅላ
ቸዋል ።

እግዚአብሔር የሌለበት ሕይወት ግን
መንፈሱ የቀዘቀዘ ነው በኑሮው ሰላም
የለውም ሕይወቱ የደረቀ ነው ይህ ችግር
ያጋጠመው ዳዊት በመዝሙር 37 ቁጥር
3 - 5 « ከኃጢአቴም የተነሣ ለአጥንቶቼ
ሰላም የላቸውም ኃጢአቴ በራሴ ላይ
ከፍ ከፍ ብሎአልና እንደ ከባድ ሸክም
በላይ ከብዶአልና » ብሏል ።

እንደተናገረውም ዳዊት ከባለጸግነት
አልፎ ታላቅ መሪ ነበር ብዙ ምቾትም
ነበረው የተመረጠ ምግብም ይመገብ
ነበር ሙቀት የሚሰጥ ልብስም ይለብስ
ነበር ። ይሁን እንጂ በዘመኑ የነበሩት ካ
ህናት የሚሰራውን ኃጢአት እያዩ ስላላ
ስተማሩትና ስላልገሰጹት መንፈሱ ቀዘ
ቀዘ በዚህም የተነሳ ሰላም አልነበረውም
አጥንቶቹም በኃጢአት ስለደረቁ ከመን
ፈስ ተራቁቶ ነበር ነገር ግን ነቢዩ ናታን
በደለኛ መሆኑንና ንሥሐ እንዲገባ አስተ
ማረው እሱም በኃጢአት የደረቁት አጥ
ንቶቹ በመንፈስ እንዲለመልሙ ከእግ

www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን በመጠየቁ የመንፈስ ተሐድሶን አገኘ ።

ይህ ከሆነ አልጫ የሆነውን የሰው ሕይወት እንደ ጨው የሚያጣፍጡ ፣ እንደ መቅረዝ ሆነው በጨለማ ውስጥ ላለው ብርሃን የሚሰጡ፣የመንፈስን ቃት እየሰጡ በእውቀትና በትምህርት የሰውን አእምሮ እየገነቡ በንስሐ የሚያድሱ የደረቀውን ሕይወት በክርስቶስ ቃል እንዲለመልምና የመንፈስ ፍሬ እንዲያፈራ የሚያደርጉ እንደ ናታንና እንደ ሕዝቅኤል ያሉ መምህራንን ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ዘመን በመብራት ትፈልጋለች ።

ነገር ግን ቅዳሴ ከመቀደስ ሌላ ለስብከተ ወንጌል ያልተዘጋጁ በቤተክርስቲያን ትምህርት ያልሰለጠኑ ቅስናና ድቁና የሚቀበሉ ካሕናት ሳያውቁና ሳይማሩ በቤተ ክርስቲያን ሙያ ሳይሰለጥኑ ስርዓተ ምንኩስና የሚፈጽሙ ሁሉ ነቢዩ ሕዝቅኤል በሸለቆ ወድቀው እንዳያቸው አጥንቶች የደረቁ ስለሆኑ እንኳንስ ለሌላው ሕይወትን መስጠታቸው ቀርቶ ለራሳቸውም ሕይወትን የሚሰጣቸው የሚፈልጉ በመሆናቸው የመንፈስ ትንሣኤ ያሻቸዋል ማለት ነው ።

ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ በትግራይ ሀገረ ስብከት ሰሚናር ካወጣው የጋራ መግለጫ ጥቂቱን እንጠቅሳለን » ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከመሥራችዋ ከኢየሱስ የተሰጠ ሕግና መመሪያ ቢኖራትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋንቋዋን በማያውቁላትና ቋንቋቸውንም በማታውቅላቸው ግብፃውያን አባቶች አባቶች ሞግዚትነት ስትኖር ይደረግ በነበረው የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ን ርስትና የመክፈልትን ቅድሚያ ለመውሰድ ሲባል በእናታቸው ጀርባ ባንቀልባ ታዝለው ለሚቀርቡት ሕፃናት ማዕረገ ዲቁና ሲሰጥ ተፈጥሮ ከሚያድላቸው ጉርምስና በቀር ምንም ዓይነት ትምህርት ሳይጨምሩ የሥራ ሳይሆን የስም ቅስና ተብቀብለው ይመለሱ እንደነበር አይዘነጋም።

አሁንም ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳትን የመሾም መብቷ ን ብትጨብጥና ቃለ አዋዲም ብታወጣም በአፈጻጸሙ ላይ ችግር ፈጥሮአል ። ድሮውንም ካሕናቱ ተልእኳቸው ምን እንደሆነ አውቀው አልተሾሙምና ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን ቃለ አዋዲ ቢያወጣውም አበው ጳጳሳት አሁንም ከግብፃውያን በወረሱት የክሕነት አሰጣጥ ጉዳይ ስለቀጠሉበት እስከ መቸውም ቢሆን ችግሩ የሚቃለል ሆኖ አልተገኘም ።

ስለክህነት አሰጣጥ ክህነት መስጠት የሚገባው በትምህርቱ ብቃት በግብረ ገብነቱ ፣ ቤተ ክርስቲያንን በትክክል የመምራት ችሎታው በምዕምናን የተመሰከረለትና በምዕመናን የተመረጠ መሆን እንዳለበት አያከራክርም ካለ በኋላ ሕጉን የሚያስከብር አባል ባለመኖሩ ማንነታቸው ያልታወቁ ወገኖች የዲቁናውንና የቅስናውን ሥልጣን ተሸክመው ሲጓዙ መታየታቸው አሳዛኝና አሳፋሪ መሆኑ ተጠቁመዋል ።

ቀጥሎም ስለ ንስሐ አባቶች ባስተላለፈው ውሳኔ በየመንግሥታዊ ድርጅቶች ተቀብለው ከነሱ የሚያገኙትን ጥቅም ብቻ በማሳደድ የቤተ ክርስቲያንን ህልውና ስለሚዘነጉ ይህ የቤተ ክርስቲያን መታደስ የእነሱን እንጀራ የሚዘጋባቸው ስለሚመስላቸው ለሰበካ ጉባኤ መቋቋም ታላቅ እንቅፋት ሆነው ተገኝተዋል ብሏል ።

በእርግጥ የሕዝቡ አንገብጋቢ ጥያቄና ለረጅም ጊዜ መፍትሔ እንደሚሆን አይጠረጠርም ለምሳሌ ወጥ የሚጣፍጠው በድስቱ ትልቅነት ፣ በመረቁ ብዛት ፣ የቅመሙ በገፍ መግባት ብቻ ሳይሆን በሠራተኛዋ የሙያ አሰለጣጠን ነው በቤተ ክርስቲያንም ስብከተ ወንጌል የሚስፋፋው ፣ ምዕመናንም የመንፈስ ዕድገት የሚያገኙት ሳይማሩ ዲቁናና ቅስና በሚቀበሉ በካሕናት ብዛት ሣይሆን በተማሩና በሰለጠኑ ጥራትና ዓይነት ባላቸው ካህናት መሆኑ መታወቅ አለበት ።

የካህናትም ተልዕኮና አገልግሎት ቀድሶ ማቁረብና ማጥመቅ ንስሐ አባትም በመሆን ብቻ አይደለም አንድ ካህን ያነበበውን ምንባብ ትርጉመ ለሁሉ እንዲገባው ማብራራትና በተጠየቀም ጊዜ መልስ መስጠት የሚችል መሆን ይገባዋል ካልሰበከ ፣ ካላስተማረ ግን የስም ካህን እንጂ የሥራ ካህን ነው ማለት አይቻልም ።

የሥራ ካህን ነው ለማለት የሚቻለው በመንፈሳ የሞቱትን የትምህርትን የዕውቀት ትንሣኤ አግኝተው እንዲነሱ የሚያደርግ ፣ የደረቁ አጥንቶችን በክርስቶስ ቃል የሚያለመልምና ወደ ሥራ ዓለም የሚቀሰቅስ እንደ ሕዝቅኤል ያለ ካህን በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ያገኘችእንደሆነ ነው ምክንያቱም ዛሬ ሰዎች ክርስቶስን ሊያዩት የሚችሉት በካህናት ሕይወት አማካኝነት መሆኑን መዘንጋት የለብንም ክርስቶስ ሲናገር « እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ » ብሏል ተከተዮቹንም ደግሞ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ብሎአቸዋል ስለዚህ ካህናት ራሳቸው ብርሃን ሆነው ሊላውን ብርሃን እንዲያደርጉ ይፈለግባቸዋልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ